የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

ዜና መጽሔት

ቁጥር 6

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

# ባንኩ ለባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት ድጋፍ አደረገ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሚያዝያ 2 ቀን 2016 ዓ.ም የተከበረውን 1445ኛውን የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ለባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት ድጋፍ አደረገ፡፡




ባንኩ ድጋፉን ያደረገው በዓሉን በማስመልከት በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል ባዘጋጀው ልዩ የበዓል መርሐ ግብር ሲሆን፣ የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው በተገኙበት ለድርጅቱ የ5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት በ2012 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ በ16 በጎ ፈቃደኛ ሴቶች ተቋቁሞ ለአምስት ዓመታት የሠራ ሲሆን፣ አሁን ላይ 4000 በላይ አባወራና እማወራ አቅመ ደካሞች ከ15 ሺሕ ልጆቻቸው ጋር በየቀኑ ይመግባል፡ ፡ 150 ተቀጣሪ ሠራተኞች ያሉት ባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት ብዙዎች በበጎ ፈቃድም ያገለግሉበታል፡፡


ጓደኞቻቸውን እና ቤተሰባቸውን አስተባብረው ድርጅቱን የመሠረቱት ወ/ሮ ሀናን ማህሙድ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለድርጅቱ የሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ በቼክ ከተቀበሉ በኋላ በሰጡት አስተያየት <<የኢትዮጵያ ልማት ባንክን በሀገርና በድርጅታችን ስም እናመሰግናለን፤ የባንኩ ማኔጅመንት በቀጣይም የበጎ አድራጎት ድርጅታችንን ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች እንዲጎበኝ እጋብዛለሁ>> ብለዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ምስጉን ተግባር የተረዳው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለግንባታ የሚሆን 5000 ካሬ ሜትር ቦታ ለድርጅቱ ማስረከቡ የተገለጸ ሲሆን፣ 2.4 ቢሊዮን ብር ለሚፈጀው ለዚህ ግንባታ ድርጅቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክንም ድጋፍ ጠይቋል፡፡

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለአራት ችግረኛ ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡

የመጀመሪያው <<ዓይነ ስውሩ ቴክኒሻን>> ሸክ መሐመድ ኑር ከሊፋ ሲሆኑ ማየት የተሳናቸው ሆነው ሳለ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ጥንቅቅ አድርገው የሚጠግኑ ባለሙያ ናቸው፡፡ ኑሯቸውን በአዋሬ አድርገው በርካታ ዓመታትን አሳልፈዋል፡፡ እኚህ የቴክኒክ ባለሙያ በቂ የመሥሪያ ቦታ ስለሌላቸውና ሥራቸውን በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት እንዲረዳቸው እንዲሁም የሥራን ክቡርነት ላሳዩበት እንደማበረታቻ የ600,000 / ስድስት መቶ ሺህ ብር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

ሌላው በግለሰብ ደረጃ ድጋፍ የተደረገው አበባ ዳባ ለተባለች በከፍተኛ የልብ ሕመም ለተጠቃችና ከፍተኛ የሕክምና ወጪ ለተጠየቀች እናት ነው፣









፡ ወ/ሮ አበባ የ3 ልጆች እናት፤ መንገድ ጠርጋ ሕይወቷን የምትገፋ ሆና ሳለ የገጠማት የልብ ሕመም ደግሞ የሕይወት ፈተና ሆኖባታል፡፡ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ብትንቀሳቀስም ለቀዶ ሕክምና 850,000 ብር ተጠይቃለች፡፡ አብዛኛውን ገንዘብ ከበጐ ፈቃድ ግለሰቦች ማግኘትም ችላለች፡፡ ሆኖም በታዝማ ሆስፒታል ቀዶ ሕክምናዋን ለማድረግ የሚያስችላት የአልጋና ሌሎች አስፈላጊ የመድኃኒት ወጪዎችን ለመሸፈን እንዲሁም ቤት ውስጥ ወደ ሙሉ ጤንነቷ እስከምትመለስ ለአንዳንድ ወጪዎች እንዲሆናት ባንኩ የ400,000 ሺህ ብር ድጋፍ አድርጎላታል፡፡

በግለሰብ ደረጃ ባንኩ ድጋፍ ያደረገላቸው በሦስት ልጆቻቸው ጽኑ ሕመም ምክንያት ከፍተኛ ችግር እና ስቃይ ውስጥ ለወደቁት አቶ አባይነህ መኩሪያ እና ወ/ሮ የትነበርሽ ጉርሙ ለተባሉ ባልና ሚስት ነው፡፡ የእነዚህ ባልና ሚስት ቤተሰብ ኑሮውን በቢሾፍቱ ልዩ ስሙ 105 ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በኪራይ ቤት፣ ለረጅም ጊዜ በብዙ ጭንቀትና ችግር ውስጥ ለማሳለፍ ተገዷል፡፡ የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ከ26 ዓመት በፊት የተወለደው ቴዎድሮስ አባይነህ መነሻ ምክንያቱን በውል ባለዩት ሕመም ተጠቅቶ ቤት መዋል ጀመረ፡፡ ከዚያም ከጊዜያት በኋላ ሁለተኛ ልጃቸው ዩናስ አባይነህ በፀና ታሞ ቤት መዋል ጀመረ፡፡ በዚህ ሲደናገጥ ለቆየው ቤተሰብ ሦስተኛ ልጃቸው ማኅሌት አባይነህም ሕመሙ አላንቀሳቀስ ብሏት ቤት መዋል ከጀመረች ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ አሁን ላይ ሦስቱም ልጆቻቸው መንቀሳቀስ የማይችሉ፣ ለመመገብም ለመፀዳዳትም የወላጆቻቸውን ድጋፍ የሚፈልጉ ሆነዋል፡፡ እናት ቤት ውስጥ እየዋሉ እድሜያቸው 26፣ 24፣ እና 21 ዓመት የሆናቸውን ልጆቻቸውን ላለፉት ስምንት ዓመታት እያስታመሙ ይገኛሉ፡፡

ከቤት ኪራይ መክፈል ብዙም የማያሻግራቸው በአባታቸው አነስተኛ ወርሃዊ ደሞዝ ላይ ብቻ የተንጠለጠለው ገቢያቸው ሦስት በጽኑ የታመሙ ልጆቻቸውን ማኖርና መንከባከብ እንዲከብዳቸው አድርጓል፡፡

ባንካችንም በከባድ የኑሮ ጫና እና የጤና መቃወስ ውስጥ ለሚገኘው ቤተሰባቸው ድጋፍ የሚሆን የ200,000 /ሁለት መቶ ሺህ /ብር፣ የቤት ሥራውን የምትሠራ የቤት ሠራተኛ በቋሚነት በወር በ3,000 ብር ሒሳብ እንዲቀጠርላቸው፣ እንዲሁም ለምግብ ቁሳቁስና ለሕክምና ወጭ በየወሩ 10,000 ብር በድምሩ በየወሩ በቋሚነት 13,000 ሺህ ብር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዝቅተኛ ደሞዝ ለሚያገኙ 7 የባንኩ ሠራተኛ የበዓል አክባሪዎች ለበግ መግዣ ለእያንዳንዳቸው 15 ሺህ ብር ድጋፍ ማድረጉም ታውቋል፡፡ ■

# ‹‹የጣፋጯ ከተማ›› ተስፋዎች

## የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠና መድረክ በቦንጋ



ቦንጋ አካባቢዋ ሲታሰብ በመዓዛና ጣዕማቸው ማራኪ የሆኑ ቅመማ ቅመሞች፣ በማር ምርት፣ በአቦል ቶናና በረካ በቃኝ የማይባለው ጥዑም ቡና፣ በአረንጓዴ ገጽታዋ፣ ጎብኚዎችን <ልኑርብሽ> በሚያስብሉ የተፈጥሮ መስኅቦቿ ትታወቃለች።

የቆዳ ስፋቱም 39,400 ካሬ ኪሎ ሜትር የሆነው፣ ከ 3,302,952 በላይ ሕዝብ እንደሚኖርበት የሚታሰበው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት በ2021 (እ.አ.አ) ጀምሮ ተመሥርቶ በ6 ዞኖች ማለትም የካፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳዎሮ፣ ምዕራብ ኦሞ እንዲሁም ኮንታ ዞኖች ሲዋቀሩ ክልሉ ከዋክብት አድርጎ ከመረጣቸው አራት ከተሞች አንዷና ዋነኛዋ ቦንጋ የክልሉ ዋና ከተማ ሆና የማገልገል ክብርን ተጎናጽፋለች።

ጣፋጭዋ ከተማ ቦንጋ የክልሉ በጎ ነገሮች ሁሉ መገለጫ ሆና የምትታይ ሲሆን፣ በዚሁ ዓመት መጋቢት ወር አጋማሽ ደግሞ ብርቅዬ የክልሉና የሀገር ልማት ተስፋዎች የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾቿን በሥልጠና ጎብኙልን ብላ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር የነበራትን የቆየ የልማት ሥራዎች ግንኙነት አጽንታለች።

### ልማት ባንክና ቦንጋ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንጋ ከተማን በሳቢ ከተማነት እንድትታይ ያበቃትን የልማት ማእከልነት በማጎናጸፍ በኩል ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ባንኩ ከበርካታ ዐሠርት ዓመታት በፊት በቦንጋና አካባቢው የልማት ሥራዎች አጋር ሆኖ ቆይቷል። የደቡብ ኢ/ህ/ክልላዊ መንግስት መደራጀትን ተከትሎ ደግሞ በአካባቢዉ ያለውን ከፍተኛ የልማት አቅምና ጸጋ ለመጠቀምና ለማሳደግ ዲስትሪክት የከፈተና በሚዛን አማን እንዲሁም ቦንጋ የቅርንጫፎችን ደረጃ ወደ ከፍተኛ ወይም ኤ-ደረጃ በማሳደግ እንዲሁም ተደራሽነቱን ለማስፋትም በቴፒ ከተማ ቢ-ደረጃ አዲስ ቅርንጫፍ በመክፈት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን፣ አሁንም በዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ቅርንጫፍ የመክፈት እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል: :

በመሆኑም ባንካችን አካባቢው በዋናነት የሚታወቅባቸውን ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ወደ ኢኮኖሚው ለማስገባት የእርሻና የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ እንዲሁም የኮንስትራክሽን እና ማእድን ማምረት ሥራዎች ብድሮችን እየሰጠ ሲሆን፤ አሁንም ከክልሉ መንግስትና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመሥራት በአካባቢው በመንቀሳቀስ የደንበኞች ምልመላን ሥራ በመሥራት ከታች በዝርዝር በተቀመጡት ዘርፎች ከ 600 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ መጠን ያላቸውን የፕሮጀክትና የሊዝ ብድር ጥያቄዎችን ተቀብሎ እየሠራ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን በክልሉ ለመሥራት የታሰቡ የልማት ውጥኖች እውን ለማድረግ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም በክልሉ ያሉ እነዚህን ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ እንዲገቡ የማነቃቃት፣ የማሠልጠን፣ በቴክኒክ የመደገፍ ቁርጠኝነቱን እያሳየ ነው። ለዚህ አንዱ ማሳያም የደ/ም/ኢ/ክ/ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ



የሐንስ ኤላሌው (ዶ/ር) - የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት



አቶ አስፋው አበራ - የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንሲንግ ምክትል ፕሬዝዳንት

በወሰደው ተነሣሽነትና በክልሉ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ለሥልጠናው ያላቸውን ዝግጅት በገለጹ ማግሥት ፈጣን ምላሽ በመስጠት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ማድረጉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም በማሳደግ ለሀገር ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክትበትንና ከባንኩ የሚሰጠውን አገልግሎት ለመቀበል በሰመረ ሁኔታ ላይ የሚገኙበትን ዐውድ ለመፍጠር በአራት ዙሮች ሲደረግ የነበረውን ሥልጠና ከሰሞኑ በደቡብ ምዕራብ ጣፋጭ ከተማ ቦንጋ በልዩ ሁኔታ አካሒዷል፡፡

ሥልጠናው ከሌሎች የሥልጠና መድረኮች ለየት የሚለው ተነሣሽነቱን የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የወሰደውና ይህም የሠልጣኞችን ፍላጎት መነሻ አድርጎ እንዲዘጋጅለት የጠየቀው በመሆኑ ነው፡፡

ይህን ተነሣሽነት በአድናቆትና በታላቅ ከበሬታ የተቀበለው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንጋ በሚገኘው ዲስትሪክቱ በኩል አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ከመጋቢት 17-21 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ እጅግ የተዋጣለት ሥልጠና አካሂዷል፡፡ በሥልጠናው ከ6 ዞኖች የተውጣጡ 664 አንቀሳቃሾች የተመዘገቡ ሲሆን 432ቱ በሥርዓት ተሳትፎ ለማድረግ የቻሉ ናቸው፤ አጠቃላይ የሥልጠናው ሂደት እንዲህ ተቃኝቷል፡፡

## የሥልጠናው ድባብ

ሥልጠናው በትልቁ የካፋ የባህል አዳራሽ የሚከናወን መሆኑ ለተካፋዮች አስቀድሞ በመነገሩ ተሳታፊዎች በማለዳ በመግቢያው ብር ላይ የተለጠፈውን የተሳታፊዎች ስም ዝርዝር በማየት የመለያ ቁጥራቸውን በማንበብ ሲጠባበቁ ቆዩ፡፡ በአዳራሹ ዋና መግቢያ በር ላይና በውስጡ የሥልጠናውን አስፈላጊነትነ እና ልዩ መሆን የሚገልጹ ባነሮች ተሰቅለዋል፡፡

ተሳታፊዎች ወደ አዳራሹ በመግባት ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ የካፋ የባህል አዳራሽ ሙዚቃ ባንድ በተለያዩ የብሔረሰቦች ቋንቋ እንኳን ደህና መጣችሁ ጣዕመ ዜማዎችን ከነውዝዋዜያቸው ለመላ ታዳሚው አቅርቧል፡፡

ከዚያም የባንኩ የሚዲያና ኮምዩኒኬሽንስ ባልደረባ በሥልጠናው አስፈላጊነት፣ ጥቅም፣ በሥልጠናው አሰጣጥና ከተሳታፊዎች ስለሚጠበቅ ሥነ ሥርዓት ገለጻ ካደረጉ በኋላ ሥልጠናውን በንግግር እንዲከፍቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንሲንግ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ አስፋው አበራ በዙም ንግግር እንዲያደርጉ ጋብዘዋል፡፡

አቶ አስፋው አበራ የሥልጠናውን ተካፋዮች <እንኳን ደህና መጣችሁ> ካሉ በኋላ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ በከፍተኛ ባለሙያዎች በተመረጡ አሠልጣኞች ይህንን ሥልጠና ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በሚሰጥበት የመርሐ ግብር መክፈቻ ፕሮግራም ላይ የባንኩን ፕሬዝዳንት ክቡር ዶክተር ዮሐንስ አያሌውን ወክለው አጠር ያለ መልእክት እንዲያስተላልፉ ስለተፈቀደላቸው አመስግነው በዚህ ለአምስት ቀናት በሚቆየው ሥልጠና ሠልጣኞች ከፍ ባለ ፍላጎትና ሥርዓት ባለው መንገድ ከሥልጠናው የሚገኘውን እውቀት እንዲቀስሙ አስገንዝበዋል፤ አቶ አስፈው መልእክት ባስተላለፉበት በዚሁ መድረክ <<ይህ ሥልጠና በእናንተው ሙሉ ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ከበርካታ ወረዳና ከተሞች የመጣችሁ የምትካፈሉበት በመሆኑ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከዚህ ሥልጠና ጊዜ ጀምሮ ከጎናችሁ የማይለይ መሆኑን ተገንዝባችሁ ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሥልጠናውን በጥንቃቄና በብስለት እንድትካፈሉ በአጽንዖት ለማሳሰብ እወዳለሁ፤ ሥልጠናው እንዲሰጥ የክልሉ ፕሬዝዳንትና ሌሎች ተባባሪ የመንግሥት አካላት ላደረጉት ትብብር ባንኩ ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል>> ብለዋል፡፡ ባንኩ እስከ አሁን ከአንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ለሚበልጡ ወገኖች ሥልጠና የሰጠ መሆኑን




አቶ ግዛው ጋጊያብ የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ የኢንተርፕራይዝና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ




ዶ/ር ኢ/ር ምትኩ በድሩ የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ ርዕሰ መስተዳድር የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ዘርፍ አማካሪ

ያስታወሱት አቶ አስፋው አበራ ይህ ክልል በማዕድን በቅመማ ቅመም በቡና በማርና በሌሎች ሀብቶች ዕምቅ ሀብት ያለው በመሆኑ ሀብቱን በመጠቀም የኢትዮጵያን ዕድገት ለማፋጠን ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር እንዲሠሩ፣ ራሳቸውን ቤተሰቦቻቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ አሳስበዋል፡፡

ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ከተላለፈው መልእክት በማስከተል የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ዘርፍ አማካሪ ዶ/ር ኢ/ር ምትኩ በድሩ ባስተላለፏቸው መልእክቶች ውስጥ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሰፊ ሀብት ያለው በመሆኑ ይህንን ሀብት አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻልና ክልሉን በተሻለ ኢኮኖሚ አሳድጎ ሥራ ፈላጊውን ኅብረተሰብ ሥራ በማስገኘት ውጤት ያለው ተግባር ማከናወን የሚገባ በመሆኑ ልማት ባንክ ገንዘቡንም መንገዱንም ይዞ የመጣ በመሆኑ በሥልጠናው ጠቃሚ እውቀት በመገብየት፣ የክልሉን እምቅ ሀብት በመጠቀም ውጤታማ ተግባር ማከናወን እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ክልሉ እንደ ሌሎቹ ክልሎች ሁሉ ከባንኩ እገዛ ለማግኘት እንዲችል ይህ ሥልጠና አስፈላጊ በመሆኑ በሥልጠናው ተጠቅመን የሚያኮራ ውጤት ለማምጣት እንችል ዘንድ ሥልጠናውን በጥሞና መከታታል እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

አቶ ግዛው ጋጊያብ የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ የኢንተርፕራይዝና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልእክት <<ክልል እንድንሆን ጠይቀን ክልል ሆነናል፤ ክልሉን ግን በልማት ለማገዝ የሥልጠናው ተሳታፊዎች አስተዋጽኦ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በቁጭት ተግተን መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከነበረበት አጣብቂኝ ወጥቶ ዛሬ በታደሰ ስሙ በርካታ አመርቂ ተግባራት እያከናወነ የሚገኝ የልማታችን የጀርባ አጥንት የሆነ ባንክ በመሆኑ አብረን ለመሥራት በቁርጠኝነት መነሣት አለብን>> ብለዋል፡፡

ከመክፍቻ ሥነሥርኣቱ በኋላ በቀጥታ የተገባው ወደ ሥልጠናው ነበር፡፡

| ዕለት | የሥልጠና ርእስ | አሠልጣኝ | አሠልጣኙ ማንነት |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ሥልጠና ቀን 17/07/2016 | ማርኬቲንግ ማኔጅመንት | አቶ ሚፍታህ ሽሞሎ | ከቦንጋ ዩንቨርሲቲ |
| 2ኛ ሥልጠና ቀን 18/07/2016 | የንግድ እቅድ አዘገጃጀትና ርእይ ቀረፃ | አቶ አበራ አጦ | ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን ማርኬቲንግ ማኔጅመንት |
| 3ኛ የሥልጠና ቀን 19/07/2016 | የንግድ እቅድ አዘገጃጀትና የሰው ሀብት ልማት | አቶ አበራ አጦ | ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን |
| 4ኛ የሥልጠና ቀን 20/07/2016 | የፋይናንሻል ስቴትመንት አዘገጃጀትና ትንተና | አቶ ጋርደው ጋንቾ | በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ እና ፋይናንስ ኮሌጅ ዲን |
| 5ኛ የሥልጠና ቀን 21/07/2016 | የብድር ፖሊሲ | አቶ ጋርደው ጋንቾ | በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ እና ፋይናንስ ኮሌጅ ዲን |
| | አነቃቂ ንግግር | መምህርት ቅድስት | በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ እና ፋይናንስ ክፍል ሃላፊ |








በሥልጠናው ማብቂያ (አምስተኛው) ቀን ያስተናገደው አንድ ልዩ መርሐ ግብር ነበር። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው መላውን የሥልጠና ተሳታፊዎች ለማግኘትና የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ በዙም የተገኙበት መድረክ ነበር። በዚህ ውይይት መድረክ ከስድስቱ የክልሉ ዞኖች የመጡ ተሳታፊዎች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ተሰብስበዋል፣ ፣ በጥያቄና መልስ ፕሮግራሙ ሠልጣኞች በጽሑፍ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መካከል ከባንኩ የብድር ፖሊሲ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በባንኩ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው ምላሽና ማብራሪያ ሊሰጥባቸው የሚፈልጉትን በመለየት በራሳቸው በጠያቂዎቹ እንዲቀርብ በዙም ጥያቄዎች እንዲመለሱና ማብራሪያ የሚፈልጉት እንዲያብራሩ ተደርጓል። ቀሪዎቹ በባንኩ ዲስትሪክት ደረጃ መመለስ የሚችሉት ጥያቄዎች በቦንጋ ዲስትሪክት ሥራ አስኪያጅ አቶ አስረስ ቦጋለ ምላሽና ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል።

ፕሬዝዳንቱ በማጠቃለያ ንግግራቸውም <<ሠልጣኞች ባገኙት እውቀት መሠረት ከልማት ባንክ በብድር የሚገኙትን ገንዘብ ለልማት አውለው አገራችንን ከድህነት ለማውጣት በሚደረገው ርብርብ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከፍተኛ ተዋናይ ሆነው ማየት የባንኩ ራእይ መሆኑን ገልጸው ይህን በማዕድን በቡና እና በቅመማ ቅመም የበለጸገውን ሀገር ሀብት ለመጠቀም እንድትችሉ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር አብረው እንዲሠሩ ካሳሰቡ በኋላ ባንኩ እናንተን ለማገልገል በሐሳብ በቴክኒክና በመሳሰሉት ድጋፉን ያለስስት የሚያደርግላችሁ በመሆኑ በባንኩ ልትጠቀሙበት ይገባል በማለት የመዝጊያ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

በሥልጠናው ለመሳተፍ ከ800 በላይሰዎች የተመዘገቡ ቢሆንም ሥልጠናው በትክክል ተከታትለው ለጣፋጭዋ ከተማና ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ተስፋ ተብለው የታሰቡት ግን 444 ብቻ ናቸው።

ሥልጠናው በክልሉ መንግሥትም ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ከመክፈቻው ጀምሮ እስከ ማጠቃለያ መርሐ ግብሩ ደረስ ከፍተኛ የሚዲያ ሽፋን አግኝቷል። የከፋ ዜና አገልግሎት የደቡብ ምዕራብ ቴሌቪዥን ሥርጭት ሰፊ ሽፋን ሰጥተዋል።

በአጠቃላይ በአምስቱ ቀናት በነበረው የሥልጠና ውሎ የሁሉም የባንኩ የቦንጋ ዲስትሪክትና ቅርንጫፍ ሠራተኞች እንዲሁም ከአዲስ አበባ የሄዱ የኮሙኒኬሽን እና የአይ.ቲ. ባለሙያዎች ከፍተኛ ተሳትፎ የተሳካ ነበር።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለተፈናቃዮች ድጋፍ አደረገ




የኢትዮጵያ ልማት ባንክም 7 ሚሊየን ብር በጀት በመያዝ ኩታበር፣ ሀርቡ፣ ጃሪና መካነ ኢየሱስ መጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች የዕለት ምግብ ድጋፍ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደሴ ዲስትሪክት ተወካይ ሥራ አስኪያጅ አቶ የኋላሸት ወርቁ ባንኩ በዋናነት የልማት ፕሮጀክቶችን ለሚያቋቁሙ ባለሃብቶች የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጥ ቢሆንም በተጓዳኝ የማኅበራዊ አገልግሎቱን የሚወጣ በመሆኑ የተፈናቃዮችን ችግር በጊዜያዊነት ለማቃለል የተደረገ ድጋፍ መሆኑን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከተያዘው 7 ሚሊየን ብር በጀት ከ4 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ በሆነ ወጭ በደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ በአራቱም መጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ለ3 ሽህ 139 ተፈናቃዮች የሚሆን የዳቦ ዱቄት፣ ድፍን ምስርና የምግብ ዘይት  ለአንድ ወር ፍጆታ የሚሆን ድጋፍ ነው ብለዋል።

በኩታበር ወረዳ ቻይና ካምፕና በሀርቡ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች መካከል ሁሴን በቀለ፣ ዚነት ፈንታውና ሌሎቹም እንደተናገሩት ማኅበረሰቡ፣ መንግስትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች እስካሁን ድጋፍ እያደረጉላቸው ቆይተዋል ይሁንና አንዳንድ ጊዜ መቆራረጥ በመኖሩ እየተቸገርን ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በተቸገርንበት ወቅት በመድረሱም ለተደረገው ድጋፍ በእጅጉ አመስግነው ሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶችም ተመሳሳይ



ድጋፍ እንዲያደርጉላቸውም በዚሁ ወቅት ጠይቀዋል።

የደቡብ ወሎ ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አሊ ሰይድ በዞኑ በመጠለያና በማኅበረሰቡ ውስጥ ከ48 ሽህ በላይ ተፈናቃዮች መኖራቸውን ገልጸው መንግስት ከሚያደርገው እርዳታ በተጨማሪ ሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተቻላቸውን ያህል የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ማድረጋቸውን አንስተው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ  ላደረገውም ድጋፍ አመስግነዋል። ■

# <<ከባንኩ ብዙ እጠብቃለሁ።>>

**ወንድዬ አበበ(ኮንታ)**



**የኢትዮጵያ** ልማት ባንክ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቦንጋ ከተማ ከመጋቢት 21 ቀን 2016 ጀምሮ በተከታታይ ለአምስት ቀናት ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ ከልዩ፣ ልዩ ዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች የተውጣጡ ቁጥራቸው በርካታ ሠልጣኞች የተሳተፉ ሲሆን፣ የኢንቨስትመንት ባለቤቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተሰማሩ ወጣቶች ታድመዋል።

ከወጣቶቹ መካከል በኪነጥበብ ሙያ ዘርፍ የተሰማራው፣ ታዋቂ ከያኒ ወንድዬ አበበ/ኮንታ/ አንዱ ነበር። ባልደረባችን አቶ ታደሰ በቀለ ስለሥልጠናውና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ሐሳቡን እንዲያካፍል ለቃለ ምልልስ ጋብዞት ነበር። እነሆ፦

ጥያቄ- እዚህ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ ነው ያገኘሁህ። ስምህን ማን ልበል?

ወንድዬ አበበ፡- ወንድዬ አበበ/ኮንታ/ እባላለሁ፤ የተወለድኩት ጅማ ከተማ መንቲና ሰፊር ነው። የኮንታ ብሔረሰብ ተወላጅ ነኝ።

ጥያቄ፡- በኪነ ጥበብ ዘርፍ አገልግሎት እየሰጠህ መሆኑን አውቃለሁ እስቲ ስለ ኪነጥበቡ ሥራህ ትንሽ አጫውተኝ፤

ወንድዬ አበበ፡- አዎ! አሁን እየሠራሁበት ያለው የሙያ መስክ በድምፃዊነት ባህላዊና ዘመናዊ ዜማዎችን በመጫወት ነው፡ ፡ በዚህ ሥራዬም በርከት ካሉ ወገኖቼ አድናቆት አግኝቻለሁ። ከሀገሬ ከኢትዮጵያም ውጪ በናይጄሪያ ሌጎሶ በተደረገው የአፍሪካ ሙዚቃ የአፍሪካ ዋንጫ ተሸላሚ ሆኜአለሁ። ዜማዎቼ በሀገር ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ ተወዳጅ እየሆኑ መጥተዋል።

ጥያቄ፡- በሙዚቃ ሥራዎችህ የተበረከተልህ ሽልማቶች ካሉህ? ብትነግረኝ

ወንድዬ አበበ፡- በማቀርባቸው የሙዚቃ ሥራዎች ከልዩ ልዩ አካላት ምስጋናዎችና ሽልማቶች ተቀብያለሁ። ዋና፣ ዋናዎቹን ንገረኝ ካልክ፤



ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር ዶክተር ዐብይ አህመድ የክብር ሰርተፊኬት በቤተ መንግስት ተቀብያለሁ፣

ሌላው በናይጄሪያ በሌጎስ ከተማ በተደረገ ውድድር ኢትዮጵያን ወክዬ በሙዚቃው ሙያዬ የአፍሪካ ዋንጫ ተሸላሚ ሆኜአለሁ።

ከኢ.ፌ.ድ.ሪ የባህልና የስፖርት ሚኒስቴር የኪነጥበብ ሽልማት ተቀብያለሁ።

ከእርቀ ሰላም ኮሚሽን የእውቅና አዋርድ ተሸላሚ ነኝ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር ፕሬዝዳንት ነኝ። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና የታክስ አምባሳደርም ነኝ።

ጥያቄ፡- ከኪነጥበብ ሙያ ዘርፍ ውጪስ ምን ምን ሙያዎች አሉህ?

ወንድዬ አበበ፡- ከኪነጥበብ ወይም ከሙዚቃ ሥራ ውጪ ስፖርት ላይ በተለይ እግር ኳስ ላይ አተኩራለሁ። ለማስታወስ፡- ለኮንታ የክልል ሻምፒዮና ደቡብ ፖሊስ ፕሪሚየር ሊግ ተሳታፊ ነበርኩ። መከላከያ 105ኛ ኮር ሻምፒዮን ሊግ፣ ሐዋሳ ከነማ፣ ወላይታ ዲቻ ክለቦች ተጫውቼ መልካም የሚባል ውጤት አስመዝግቤያለሁ።

ጥያቄ፡- ስልጠና እየወሰድክ ነው፤ ስልጠናው ደግሞ በባንኩ ፖሊሲ መሠረት ላቀረባችሁት ሥራ ማከናወኛ ይሆን ዘንድ ብድሩን ከወሰዳችሁ በኋላ አጠቃቀሙንና አመላለሱን በተመለከተ የሚሰጥ ነው። አንተ ከሙዚቃው ሥራ ልትወጣ አሰብክ እንዴ?

ወንድዬ አበበ፡- ከሙዚቃው አልወጣም፤ ሙዚቃ መሸጋገሪያ እንጂ የዘለአለም መኖሪያ አድርጌ አልወሰደውም። ሙያውን እጅግ አከብራለሁ፡፡ በተጓዳኝ የምሸራው ሥራ ስለአለ ነው?

ጥያቄ፡- ይህ ተጓዳኝ ሥራ ምንድን ነው?

መልስ፡- ብዙ ሐሳብ አለን፤ የፊልም ሥራ ነው። የፊልም ኢንዱስትሪ በኅገራችን ለማስፋፋት ኤኮ ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ ቶካ የፊልም መንደር ለመገንባት እና በአፍሪካ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት እዚሁ ደቡብ ምዕራብ ክልል ኮንታ ውስጥ ብሔራዊ ፓርክ ለመገንባት ከሪቦራ ሐይቅ ዳርቻ ላይ 43,000 ካሬ ሜትር ቦታ በመረከብ ሥራ ጀምረናል።

ጥያቄ፡- ብቻህን ነው ወይስ የሚረዱህ አጋሮች አሉህ?

መልስ፡- ብቻዬን አይደለሁም፤ ፕሮጀክቱ ሰፊ በመሆኑ ሰፊ ሀብት ይፈልጋል። ስለሆነም ኃ/የተ/የግ/ማህበር አቋቁመን ለመሥራት አቅደናል።

ጥያቄ፡- ምን ያህል ጉዞው እስከአሁን ተሳክቶላቸዋል?

ወንድዬ አበበ፡- በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፤ ተስፋ ሰጪ ጀምሮ ላይ ነን ያለነው። ክልሉ እየተባበረን ነው ያለው።

ጥያቄ፡- ከክልሉ መንግስት ፈቃድ አግኝታችኋል?

ወንድዬ አበበ፡- አዎን አግኝተናል።

ጥያቄ፡- በተሰጣችሁ ሰፊ ቦታ ምን፣ ምን ትሠሩበታላችሁ?

ወንድዬ አበበ፡- ብዙ ሥራ እንሠራበታለን፤ ለምሳሌ፡ ኮንታ ጨበራ፡ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ከርቦራ ሐይቅ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ነው። ዓሣ እንዲረባ እናደርጋለን። የሐይቅ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ነው። የሐይቅ ላይ ጀልባ መዝናኛ ይኖረናል። ቱር ኤንድ ትራቭል የመሳሰሉ የሥራ ዘርፎች ይኖሩናል። ይህ ሲሳካ በርካታ ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን በሥራ እያሳተፍን የክልሉን ምጣኔ ለማሳደግ ጥረታችንን እንቀጥላለን።

ጥያቄ፡- የባንካችን ሥልጠናው እንዴት ነበር?

ወንድዬ አበበ፡- ሥልጠናው እጅግ በጣም የረካሁበት ነው። አሠልጣኞች እውቀታቸውን ያለስስት ያካፈሉበት፣ ሠልጣኞች ያቀረቧቸው ሐሳቦች የአንዱ ለአንዱ ትምህርት የሆነበት፣ የልማት ባንክን አሠራር የተረዳንበት በአጠቃላይ ከፍተኛ እውቀት የቀሰምንበት ነበር።

ጥያቄ፡- በመጨረሻ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምን ትጠብቃለህ?

ወንድዬ አበበ፡- ከባንኩ ብዙ እጠብቃለሁ። ባንኩ የምናቀርበውን ፕሮፖዛል ተመልክቶ፣ የሙያ ድጋፍ አድርጎ፣ ጠቃሚነቱን ተገንዝቦ የባንኩ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሠረት በሚሰጠን ብድር የታሰበው ፕሮጀክት እውን እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንዲያደርግልን ነው።



# የሁለቱ ብርቅዬ ተቋማት አጋርነት፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ትግስቱ አምሳሉ ከሌሎች የሁለቱ ተቋማት የማኔጅምንት አባላት ጋር በመሆን መጋቢት 20 ቀን 2016 ዓ.ም ቢሾፍቱ የሚገኘውን የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ኢንስቲቱዩት ጎብኝተዋል፤ የተቋሙ የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር በሬቻ ባይሳ በተገኙበትም ከተቋሙ ሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።

የእንስሳት ሀብት ልማትና ምርታማነትን ለማሻሻል በእንስሳት ጤና ላይ ጥናቶችን በማድረግ፣ ምርመራና በሽታ ቁጥጥር ላይ በመሥራት ሥልጠናና ማማከር አገልግሎትን በመስጠት ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ያለ ተቋም ነው፣ ፡ ተቋሙ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ባላቸው ባለሙያዎቹ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ውጤታማ፣ ብቁና ተደራሽ አገልግሎት ለመስጠትም እየተጋ ነው። የተቋሙ ሚና የኢትዮጵያን የእንስሳት ሀብት በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆን ማስቻል ነው።

ከተመሠረተ ከ60 ዓመታት በላይ የሆነው ብሄራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲቲዩት በዚህ ተልእኮው ላይ ተመሥርቶ በምርምር የታገዘ የመድኃኒትና የተለያዩ ክትባቶችን የማምረት ሂደት ዋነኛ ሥራው ነው። በ7 ላብራቶሪዎች የተደራጀው ተቋሙ በውስጡ የእንስሳት መድኃኒት ማቀነባበሪያ የያዘ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት ከ12 ዓይነት በላይ የእንስሳት መድኃኒቶችን የማምረት አቅም ገንብቷል።

ከዚህም በተጨማሪ ከ23 በላይ የክትባት ዓይነቶችን በማምረት እንደ ሀገር በእንስሳት ላይ የሚከሰቱ ወረርሽኞችን በመከላከል ላይ ይገኛል። በአሁን ወቅት በዓመት ከ350 ሚሊዮን ዶዝ በላይ ክትባት እያመረተ ይገኛል።

ተቋሙ ከዚህም በላይ ጠቃሚ ዕቅዶች ቢኖሩትም የፋይናንስ እጥረት በተፈለገው ልክ እንዳይንቀሳቀስ እንዳደረገው ይጠቆማል።

እንዲህ ላሉ ለሀገር ልማት ቁልፍ ሚና ላላቸውና በመንግሥት ትኩረት በተሰጣቸው የልማት ዘርፎች ላይ ለተሰማሩ ተቋማት አጋር በመሆን የሚታወቀው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የተቋሙን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለመጎብኘትና አለብኝ በሚላቸው ውስንነቶች ላይ ለመምከር ወደ ተቋሙ ተንቀሳቅሷል።

ልማት ባንክ እያካሄደ ባለው ሰፊ የሪፎርም ተግባራት በግብርና ዘርፉ በእንስሳት እርባታና በዶሮ እርባታ ላይ የሚሠሩ ራሳቸውን የቻሉ ዳይሬክቶሬቶች አቋቁሞ በዘርፉ ውጤት እንዲመዘገብ በሊዝ ፋይናንስና በፕሮጀክት ፋይናንሲንግ አገልግሎቶቹ የኢንቨስተሮች አጋርነቱን እያሳየ በመሆኑ ለዚህ ዘርፍ ቁልፍ ሚና ከሚጫወተው የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ኢንስቲቱዩት ጋር አብሮ የመሥራት ፍላጎቱን በሥራ ኃላፊዎቹ ጉብኝትና ውይይት መድረክ አረጋግጧል።

በተዘጋጀው ውይይት መድረክ ስለተቋሙ ማብራሪያ የሰጡት ዶ/ር በሬቻ ባይሳ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በትብብር በመሥራት በሀገር አቀፍ ደረጃ የእንስሳት በሽታን ለመከላከልና ለዚሁ ዓላማ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገዙ የእንስሳት መድኃኒቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ሀገሪቱ የምታወጣውን ወጭ ለማስቀረት መታቀዱንም ገልጸዋል፡ ፡ በተጨማሪም የሚያመርቷቸው መድኃኒቶች በመንግሥት ተቋማትና የክልል የግብርና ቢሮዎች አማካኝነት እንደሚሰራጩ የገለጹ ሲሆን፣ ተቋሙ በሽያጭ አኳያ ትርፋማ መሆኑን አመላክተዋል። ከሀገር ውስጥ ገበያ ባሻገርም ከ23 ለሚበልጡ የአፍሪካ ሀገራት የእንስሳት መድኃኒት እንደሚያሰራጩ የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ ባለፈው 1 ዓመት ካመረቱት ምርት ውስጥ 79 በመቶውን ለሀገር ውስጥ ገበያ እንዲሁም 21 በመቶ ለውጭ ገበያ ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

በዘርፉ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖርም ተቋሙ ማምረት ከሚችለው ከግማሽ በታች እያመረተ የሚገኘው በፋይናንስ እጥረት መሆኑን ጠቅሰው ተቋሙን







በፋይናንስ ለማገዝም የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ለመክፈት ዝግጅት መጠናቀቁንም አመላክተዋል፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ዋና ዳይሬክተሩ ጠይቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው ኢንስቲቲዩቱ እንደ ሀገር በብቸኝነት ውጤታማ ሥራ እየሠራ መሆኑን አድንቀው፤ ተቋሙ እየሠራ ያለው ሥራ የውጭ ምንዛሬን ከማስቀረትም ባሻገር በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ መሆኑም ከጠቀሜታዎቹ መካከል መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሪፎርም ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በም/ፕሬዝዳንትነት ደረጃ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ የጠቆሙት ዶ/ር ዮሐንስ ተቋሙም በዚሁ ዘርፍ የሚሠራ በመሆኑ በጋራ መሥራት የሚቻልባቸው መንገዶች መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

ባንኩ በቅርቡ በጀመረው የጤናና የቱሪዝም አገልግሎት ስርም በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ መድኃኒቶች በጤናው ዘርፍ ፋይናንስ ማድረግ ስለጀመረ ተቋሙ ባንኩ የሚጠይቀውን መስፈርት ማሟላት ከቻለ አገልግሎቱን መጠቀም እንደሚችል አረጋግጠዋል፡፡

የሁለቱ ተቋማት ተቆጣጣሪ የሆነው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ተወካዮችም በውይይቱ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

መንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ትግስቱ አምሳሉ ተቋሙ እንደሀገር በእንስሳት ጤና ዘርፍ እውቀጥ እንዲያድግ በቂ ግንዛቤ ፈጥሮ የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ማድረጉን የጠቀሱ ሲሆን ያለበት የፈይናንስ ችግር ቢቀረፍ በርካታ ስራዎችን መስራት እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

ኢኒስቲትዮቱ እንደ አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ከባንክ ጋር መስራት እንደሚችል ያመላከቱት አቶ ትግስቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክም እገዛ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በኢትዮጵያ በቸኛው ልማት ባንክ ሲሆን፣ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ተቋምም በሀገሪቱ ብቸኛ የእንስሳት ጤና ተቋም መሆኑ ሁለቱን ተቋማት ብርቅዬ ያደርጋቸዋል፡፡

# ከሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች የማሽነሪ ርክክብ ተደረገ




**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለሊዝ ፋይናንስ ደንበኞቹ ሐሙስ መጋቢት 5 ቀን 2016 ዓ.ም በሞኤይንኮ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ግቢ በመገኘት የማሽነሪ ርክክብ አካሄደ።**

ባንኩ በሞኤይንኮ እና ወረታ ኢንተርናሽናል አቅራቢዎች አማካኝነት ያቀረባቸው 10 የኮምባይን ሃርቨስተሮች 167 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገባቸው እንደሆኑ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንሲንግ ም/ፕሬዝዳንት አቶ አስፋው አበራ በርክክብ ወቅት ባደረጉት ንግግር አስታውቀዋል።

በዚሁ የርክክብ ሥነ ሥርዓት መልእክት ያስተላለፉት አቶ አስፋው አበራ አክለውም <<የግብርና ዘርፉ በተሻለ ምርታማ እንዲሆን በዘመናዊ የግብርና ግብዓቶች መታገዝ ይኖርበታል፤ ይህን ለማሳካትም ባንኩ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው>> ብለዋል።

የአጭዶ መውቂያ ማሽኖቹ የምርት ብክነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንሱ፣ የአርሶ አደሩን ድካም የሚያቃልሉ፣ወጪን የሚቀንሱ ከመሆናቸውም በላይ በአጭር ጊዜ በርካታ የሰብል ምርትን በማጨድና በመውቃት ዘርፈ ብዙ ጥቅም የሚሰጡ መሆናቸውም በርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ ተገልጿል። ■








# ጥቂት ነጥቦች ስለዓለም ባንክ

**የዓለም ባንክ** የተቋቋመው እ.አ.አ. በ1944 ሲሆን፣ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ አውሮፓና ጃፓንን በመልሶ ግንባታ ለመታደግ የተቋቋመ ነበር። ሲመሠረት የነበሩት አባል ሀገራት 38 ነበሩ፤ አሁን ላይ የዓለም ባንክ በ186 ሀገራት ባለቤትነት የተያዘ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም ነው።

አሁን ላይ በትውልድ ሕንዳዊ በዜግነት አሜሪካዊ በሆኑት አጀ ባንጋ የሚመራው የዓለም ባንክ ግሩፕ ከ70 በላይ በሆኑ የዓለም ሀገራት ውስጥ ይሠራል። ዋና መሥሪያ ቤቱን በዋሽንግተን ዲሲ ያደረገው የዓለም ባንክ በዓለም ውስጥ 120 ጽሕፈት ቤቶች (offices) 10,000 የሚደርሱ ሠራተኞች አሉት።

የባንኩ ሥራ ድህነትን ለመቀነስ ለሚያስችሉ የአባል ሀገራት ፕሮጀክቶች ብድር በማቅረብ የኑሮ ደረጃን የማሻሻል፣ ልማትን የማፋጠን ሚና አለው።

ባንኩ ግዙፍ የጥናት ማእከል አለው። ከጥናቶቹ የሚገኙ ውጤቶችን የልማት እውቀቶችን መሠረት ያደረጉ የማማከርና የመደገፍ ሚና ያለው ሥራ ክፍልም አለው። በማእከሉ የሚሠሩ ጥናቶች በፋይናንሲንግ አገልግሎት፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ሥነ ምግብ፣ ፍትሕ፣ ሕግ፣ አካባቢ ጥበቃ ዘርፎች ላይ ያተኩራሉ።

ባንኩ የዓላም ባንክ ተቋም የሚባል የሥልጠና ማእከልም አለው። የአባል ሀገር መንግሥታትን እና ሌሎችምን ባለሥልጣናት በማሠልጠን ይታወቃል።

የዓለም ባንክ በውስጡ ልዩ ተልእኮ ይዘው በንቃት የሚሠሩ ተቋማት አሉት። በዚህም ምክንያት እነዚህ ተቋማት በጥቅል የዓለም ባንክ ግሩፕ ተብለው ይጠራሉ።

- IBRD - ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሀገራት የሚያበድር ነው።
- IDA - ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሀገራት የሚያበድር ነው።
- IFC - ለግሉ ሴክተር የሚያበድር ነው።
- MIGA - የግል ኩባንያዎች በውጪ ሀገራት መዋእለ ንዋይ እንዲያፈሱ የሚያበረታታ ነው።
- ICSID - የግል ባለሀብቶች እና ውጪ ሀገራት ባልተስማሙባቸው ጉዳዮች ላይ የበለጠ ተወያይተው እንዲሠሩ ድጋፍ የሚሰጥ ነው።

አባል ሀገራት እንደ ኢኮኖሚያቸው መጠን በባንኩ ውስጥ ሼር ያላቸው ሲሆን፣ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ እጅግ ሰፊውን ድርሻ ይዛለች፤ ጃፓን፣ ጀርመን፣ ዩናይትድ ኪንግደም እና ፈረንሳይ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከፍተኛ የሼር ድርሻ አላቸው።

ባንኩ የሚያበድረውን ገንዘብ የሚያገኘው በዓለም ላይ ካሉ የካፒታል ገበያዎች በዝቅተኛ ወለድ ምጣኔ በመበደር ነው። ባንኩ ለመበደር የሚያበቃውን አቅም ካለው ሰፊና በአግባቡ ከሚመራ የገንዘብ ክምችቱ ያገኛል። የገንዘብ ክምችቱን የሚሰበስበውም ከገንዘብ ገበያው ከሚገኝ ፈንድ፣ ከአባል ሀገራት ክፍያ እና አስተዋጽኦ (በተለይ ከሀብታም ሀገራት) ከራሱ ኢንቨስትመንቶች ከሚያገኘው ገቢ፣ ከአባል ሀገራቱ ከሚያገኘውም ብድር ነው።

ባንኩ መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሀገራት የሚያቀርበው ብድር ንግድ ባንኮች



ከሚያቀርቡበት ወለድ ምጣኔ ዝቅተኛ ሆኖና ከንግድ ባንኮች በተሻለ በረጅም ጊዜ ክፍያ እንዲመለስ በማድረግ ነው።

## የዓለም ባንክ ብድር፦

- ሀገራትን ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እንዲያቀርቡ፣
- ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ፣ መምህራንን እንዲያሠለጥኑ፣
- የግብርና ምርታማነት እንዲጨምር፣
- ደንና የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ እንዲተዳደሩ፣
- የቴሌኮምዩኒኬሽንስ ኔትዎርክን ለማስፋፋት ኃይል ለማመንጨትና ለማሠራጨት፣
- የጤና እንክብካቤን ለማስፋፋትና ዘመናዊነትን ለማጠናከር ብድር ይሰጣል።

THE WORLD BANK

ፕሮጀክቶች በሀገራቱ ፍላጎት እቅድና ብድር ጥያቄ የሚጀመሩ ሲሆን፣ የባንኩ ሠራተኞች ከተበዳሪ ሀገራት የሚቀርቡትን ፕሮጀክቶች ከተለያዩ አንጻሮች ይገመግማሉ። ለሀገሩ ኢኮኖሚ ካላቸው ፋይዳ፣ ለድህነት ቅነሳና ለሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከሚሰጡት ዕድል፣ ለአካባቢ ጥበቃ አሁንና ለቀጣይ ዘመናት ከሚኖራቸው ተጽእኖ፣ ደጋፉ ሲጠናቀቅ ተበዳሪው ሀገር የተጀመረውን ፕሮጀክት ወደፊት ከማራመድ አቅሙ፣ ሌሎች የብድር ምንጮች ሊገኙለት ከመቻላቸው ወይም ካለመቻላቸው አንጻር ይገመገማል። ከዚያ በኋላ በሚደረጉ ጠንካራ ድርድርና ውይይቶች በኋላ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበትን ብድር ባንኩ ያቀርባል።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
# ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት

## I. የሀብት ማሰባሰብ
(Resource Mobilization)

**ሱኩክ ዋካላ**

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለተወሰኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ወይም ባለሀብቶች (restricted Investors) ብቻ ታሳቢ አድርጎ የነደፈው እና የሸሪዓ መርሆችን የተከተለ ቦንድ ፤

**ሙዳራባህ**

የኢንቨስትመንት ተቀማጭ ሒሳብ፤

**ወዲዓ የተንቀሳቃሽ ሒሳብ**

ለፋይናንሲንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች፤

**ወዲዓ የቁጠባ ሒሳብ**

ለባንኩ ሠራተኞች፤

## II. የፋይናንሲንግ አገልግሎቶች
(Financing Services)

**ኢጃራ**

ከወለድ ነጻ የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት፤

**ሙራበሐ**

ከወለድ ነጻ የፕሮጀክት ፋይናንሲንግ አገልግሎት፤

ጆሴፍ ብሮዝ ቲቶ መንገድ
+251 11 551 1606
+251 11 551 1188/89
1900

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
የልማት አጋርዎ !